DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

## ዲሲፒኤስ ለሁለተኛ ደረጃ እና ለኮሌጅ ትምህርት መንታ ምዝገባ ፕሮግራም
## የተማሪ/ወላጅ ማረጋገጫ እና መረጃ ይፋ እንዲወጣ የመፍቀጃ ቅጽ
## (DCPS DUAL ENROLLMENT PROGRAM STUDENT/PARENT VERIFICATION AND RELEASE OF INFORMATION FORM)

ለዲሲፒኤስ ሁለተኛ ደረጃ እና ለኮሌጅ ትምህርት መንታ ምዝገባ ፕሮግራም፣ ለማመልከት፣ ተማሪው በተሳታፊ ዩንቨርሲቲ ለመንታ የምዝገባ ፕሮግራም ለመቀበል ከመታሰቡ በፊት ይህ ቅጽ ተጠናቆ መሞላት እና በኦን ላይ የመንታ ምዝገባ ማመልከቻ (uploaded to the online dual enrollment application) ላይ መጫን ይኖርበታል። ይህ ቅጽ የግል መለያ የሆኑ መረጃዎችን የሚይዝ እንደመሆኑ መጠን፣ እባክዎን ሠነዱን ኤሜይል አያድርጉ **(not email)** ።

የተማሪው ስም፤ ______________________________ ______________________________

የመጀመሪያ ስም — የመጨረሻ ስም

የሁለተኛ ደረጃው ትምህርት ቤት ስም፤ ______________________________

---

<u>ክፍል **1**፤ ለአመልካች ተማሪዎች ሁሉ መመሪያ፤</u>

እባካህን ከዚህ በታች የሰፈረውን የእያንዳንዱን መግለጫ ፍሬ ሀሳብ በማንበብ ለዲሲፒኤስ የመንታ ምዝገባ ፕሮግራም ከማመልከት ጋር በየዐረፍተ ነገሩ ለተገለጹ ነጥቦች የተዛመዱትን የምትገንዘብ መሆኑን ለማመልከት አጭር ምልክት አድርግባቸው። እድሜህ ከ 18 ዓመት በታች ከሆነ፣ ወላጅህ ወይንም ህጋዊ አሳዳጊህም ከዝህ በታች የሰፈሩትን ነጥቦች ማንበብ፣ አጭር ምልክት ማድረግ እና "የወላጅ/የህጋዊ አሳዳጊህ ስምምነት" በሚለው ክፍል ላይ መፈረም አለበት። አመልካቾች ሁሉ በዚህ ክፍል ያለውን አጠናቀው መሙላት አለባቸው።

የተማሪ ስምምነት መግለጫ **(**እባክህን ከዚህ በታች በእያንዳንዱ ላይ ምልክት አድርግ**)**

እንደ ዲሲፒኤስ የመንታ ፕሮግራም አመልካች፤

- ☐ የማመልከቻዎቼ አካል የሆኑ እንደ የግላዊ መለያ (demographic information)፣ መረጃዎችን፣ የመገናኛ መረጃዎች እና የድጋፍ ማስረጃዎቼ ጭምር እና እንዲሁም የትምህርት ማስረጃ ምስክር ወረቀቶቼ እና የፈተና ውጤቶቼን ጨምሮ በኦን ላይን ማመልከቻየ ላይ ላሰፍርኳቸው ዩንቨርሲቲዎች እንዲላኩ ይደረጋሉ።
- ☐ በአንድ ጊዜ ከአንድ በበለጠ የመንታ ትምህርት ምዝገባ ፕሮግራም ላልሳተፍ እችላለሁ።
- ☐ ለዲሲፒኤስ የመንታ ምዝገባ ፕሮግራም ለመሳተፍ ከተመረጥኩ፣ ለዚህ ፕሮግራም በምማርባቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ዩንቨርሲቲ ያሉትን ሥርዓት፣ ደንብ፣ ሥነ ምግባር እና ህጎችን ጨመሮ ማክበርና መከተል እንደሚኖርብኝ ዐውቃለሁ።
- ☐ ከመንታ ምዝገባ ኮርሶች ምዝገባ ለመውጣት ብፈልግ፣ ጉዳዩን ለትምህርት አማካሪዬ፣ ለዲሲፒኤስ እና ዩንቨርሲቲ አስተባባሪ በጽሁፍ ማስታወቅ እንዳለብኝ ዐውቃለሁ። በተጨማሪም፣ በዩንቨርሲቲው መደበኛ ከኮርስ የመላቀቂያ ሂደትን ማጠናቀቅ አለብኝ።
- ☐ በዲሲፒኤስ የመንታ ምዝገባ ፕሮግራም ተቀባይነት ማግኘት፡ በኋላ በማናቸውም ኮሌጅም ሆነ ዩንቨርሲቲ የመግቢያ ዋስትና እንደማይ ሆን እረዳለሁ።
- ☐ የቤተሰብ የትምህርት መብቶች (Family Educational Rights) እና የግል መብት ጥበቃ ደንብ (Privacy Act (FERPA)) የት ምህርት ማስረጃዎችን በሚመለከት የተወሰኑ መብቶችን ለተማሪዎች እንደሚሰጥ ይገባኛል። የተማሪ የት ምህርት ማስረጃዎች በምሥጢር ተጠብቀው እንደሚያዙ እና ለዲሲፒኤስ መንታ ምዝገባ ማመልከቻ እና OSSE በኦን ላይን ላይ ከመረጥኳቸው ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቴ እና ከዩንቨርሲቲዎች ባሻገር ያለ እኔ የጽሁፍ ፈቃድ ለሌላ ለሦስተኛ አካል አይሰጡም።

---

ከዚህ በታች በመፈርም፣ በአቀባበል ሂደት ውስጥ የተካተቱ መረጃዎች ሁሉ፣ የአቀርብኳቸው ማመልከቻውን፣ ሀተታ ድርሰቴን፣ እና የድጋፍ ማስረጃዎቼን ጨምሮ የእኔው የራሴ እንደሆኑን እና በእውነተኛነት እና ሀቀኛነት ላይ ተመሥርተው የቀረቡ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ። በተጨማሪም፣ ከዚህ በላይ ተዘርዝሮ በተመለከተው መሠረት፣ ለፕሮግራሙ ብቁነት ለእጩነቴ መገምገሚያነት እንዲያገለግል፣ ከዚህ ቀጥየ ዲሲፒኤስ ማመልከቻየን በተመለከተ በዲሲፒኤስ ለመንታ ምዝገባ ፕሮግራም ማመልካቻ ለመረጥኳቸው ዩንቨርሲቲዎች እንዲስጥ ሥልጣን ሰጥቻለሁ። ለሌሎች አካላት እንዲሰጡ የፈቀድኳቸውን እነዚህን መረጃዎች በመርመር የይዞቶቻቸውን ሁኔታ ለመጥየቅ እና ለማጣራት በተሰጠው ሥልጣን እና መብት መሠረት፣ በማንኛውም ጊዜ የማይመስሉኝ መረጃዎች ይፋ እንዳይ ወጡ በጽሁፍ ማገድ እና መከልከል እንደምችል ዐውቃለሁ።

በጉልህ የተጻፈ የተማሪ ስም፤ ______________________________

የተማሪው ፊርማ፤ ______________________________ ቀን፤ ____________________

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

**ክፍል 2፤ የ ወላጅ/የህጋዊ አሳዳጊ ስምምነት (እድሜአቸው ከ 18 ዓመት በታች ለሆናቸው ወጣቶች)**
(እባክዎን ከዚህ በታች በተመለከቱት በእያንዳንዱ ሀሳብ ላይ እጭር ምልክትዎን ያስፍሩ)

በዲሲፒኤስ የመንታ ምዝገባ ፕሮግራም ለመሳተፍ እንደ ተማሪ ልጄ አመልካችነቴ፣ በሚከተሉት ሀሳቦች እስማማለሁ።

☐ የተማሪየ ማመልከቻ የትምህርት ማስረጃዎች አካል የሆኑ እንደ የግላዊ መለያ (demographic information)፣ መረጃዎችን፣ የመገናኛ መረጃዎች እና የድጋፍ ማስረጃዎቼ ጭምር እና እንዲሁም የተማሪየ የትምህርት ማስረጃ ምስክር ወረቀቶቼ እና የፈተና ውጤቶቼን ጨምሮ በኦን ላይን ማመልከቻየ ላይ ላሰፍርኳቸው ዩንቨርሲቲዎች እንዲላኩ ይደረጋሉ።

☐ ተማሪየ በአንድ ጊዜ ከአንድ በበለጠ የመንታ ትምህርት ምዝገባ ፕሮግራም ላይ ላይሳተፍ ይችላል።

☐ ለዲሲፒኤስ የመንታ ምዝገባ ፕሮግራም ለመሳተፍ ከተመረጠ፣ ተማሪየ በሚማርባቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ዩንቨርሲቲ ያሉትን ሥርዓት፣ ደንብ፣ ሥነምግባር እና ህጎችን ጨመሮ ያከበራል፣ ይከተላል።

☐ ከዮንቨርሲቲ ኮርስ ተማሪየ ለመውጣት ከፈለገ፣ የትምህርት አማካሪውን፣ የዲሲፒኤስ አስተባባሪውን እና የዩንቨርሲቲ አስተባባሪውን በጽሁፍ ማስታወቅ እንዳለበት ዐውቅላሁ። በተጨማሪም፣ ተማሪየ መደበኛውን በዩንቨርሲቲ ከኮርስ የመ ውጫ ሂደትን ማጠናቀቅ እንዳለበት ዐውቃለሁ።

☐ በዲሲፒኤስ የመንታ ምዝገባ ፕሮግራም መመዝገብ፣ በኋላ በየትኛውም ኮሌጅ ወይንም ዩንቨርሲቲ፣ ለተማሪ የመቀበል እድል ዋስትና አይሆንም።

☐ የቤተሰብ የትምህርት መብቶች (Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)) እና የግል መብት ጥበቃ ደንብ (Privacy Act (FERPA)) የትምህርት ማስረጃዎችን በሚመለከት የተወሰኑ መብቶችን ለተማሪዎች እንደሚሰጥ ይገባኛል። የተማሪ የትምህርት ማስረጃዎች በምሥጢር ተጠብቀው እንደሚያዙ እና ለዲሲፒኤስ ለመንታ ምዝገባ ማመልከቻ እና OSSE በኦን ላይን ላይ ከመረጥኳቸው ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቴ እና ከዩንቨርሲቲዎች ባሻገር ያለ እኔ የጽሁፍ ፈቃድ ለሌላ ለሦስተኛ አካል አይሰጡም።.

☐ እንደ ወላጅነቴ ወይንም ህጋዊ አሳዳጊነቴ፣ ተማሪየ በዲሲፒኤስ ለመንታ ምዝገባ ፕሮግራም ተሳትፎ ከተመረጠ እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማት በላይ ባሉ (ይህም በኮሌጅ ወይንም ዩንቨርሲቲ) ከተመዘገበ፣ በ FERPA መሠረት ለተማሪየ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ባለ ተቋም የተያዙትን ማናቸውንም መረጃዎች ሁሉ የመያዝ እና የማንቀሳቀስ መብትን በሚመለከት ከእኔ ወደ ተማሪ ልጄ የሚተላለፍ ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ ተማሪየ ከ 18 ዓመት እድሜ በታች ከሆነ በድኅረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋም ወደ ልጄ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተላኩ የትምህርት ማስረጃዎችን በ FERPA ሥር የመመርመር እና የማጣራት መብቶቼ የተጠበቁ ይሆናል።

---

|ከዚህ በታች በፈረም፣ ከላይ በተገለጸው መሠረት፣ ዲሲፒኤስ ለፕሮግራሙ የእጩነቴን ብቃት ለመገምገሚያ አገልግሎት ተግባር እንዲውል፣ በኦን ላይን ማማልከቻው ላይ ለተመለከተው ዩንቨርሲቲ ተማሪየን የሚመለከቱ ማናቸውንም መረጃዎች ሁሉ እንዲሰጥ ሥልጣን ሰጥቻለሁ። እነዚህም መረጃዎች በቃል፣ በኤሌክትሮኒክስ ወይንም በወረቀት ማለትም በጽሁፍ ሊለቀቁ እንደሚችሉ ይገባኛል። በዚህ ፈቃድ መስጫ መሠረት፣ የእነዚህን መረጃዎች ይዘት ለመመርመር መብት እንዳለኝ እና በማናቸውም ጊዜ ስምምነቱን የማገድ ሥልጣን እንዳለኝ እገነዘባለሁ። በተጨማሪ፣ ከላይ የተጠቀሰው ተማሪ ወላጅ/ አሳዳጊ እንደሆንኩ አረጋግጣለሁ።

የወላጅ/የህጋዊ አሳዳጊ በጉልህ የተጻፈ ስም፤ ______________________________

የወላጅ/የህጋዊ አሳዳጊ ፊርማ፤______________________________ ቀን፤ ____________________

---

ጥያቄዎች አሉዎት? እባክዎን ከ Emily Huey ጋር በ emily.huey@k12.dc.gov ይገናኙ።